# ስለ ጋብቻ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

አመሠራረቱ፦ በኦሪት ዘፍጥረት ፩፥፳፯ ላይ እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ወንድና ሴት አድርጎ እንደፈጠረው ይገልጻል። ምዕራፍ ፪፥፲፰ ደግሞ ሰው ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም አይደለምና ሴት እንፍጠርለት ይላል። በምዕራፍ ፪፥፳፪-፳፭ ለአዳም እርሱን የሚመስልና እርሱን የሚያስደስት ፍጥረት ሌላ አልተገኘለትም ይላል።

እነዚህ አባባሎች አንድ ብቸኛ የሆነውን ሰውን አንድ ሌላ ረዳት እንዳስፈለገው፣ ያለዚያች ረዳት ደግሞ ከባድ እንደሆነ ያስተምረናል። እነዚሁ ዓረፍተ ነገሮች በደምብ ሲመረመሩና ሲታዩ ሰው ከሌላው ፍጥረት ለየት ያለና ብርቱ ጥንቃቄ የተደረገለት መሆኑንም ያስተምራሉ። ከዚህ በተጨማሪ የአዳምን ብቸኝነት በዙሪያው ያሉ የእንስሳትና የአራዊት ክምችት፣ የገነት መዓዛና ፍራፍሬዎች ባዶነቱን ሊሞሉ ወይም ደስታ ሊሰጡት አልቻሉም። ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው ሁሉም ፍጥረታት ከተቃራኒ ጾታ ጓደኞቻቸው ጋር ሲጫወቱ ለአዳም ምንም ዓይነት የደስታውም ሆነ የኃዘኑ ተካፋይ ሊሆኑለት አልቻሉም። እነሱን ትክ ብሎ ከማየት በስተቀር ምንም አልፈየዱለትም። በዚያ ፈንታ ይልቅ እነዚያ ሲጫወቱና እሱን ሲያስደስቱት የዋሉት ፍጥረታት ሁሉ ወደየማደሪያቸው ሲጓዙ አዳም ብቻውን ፍግግ ብሎ መቅረት ብቻ ሆነ። ይሄ ብቸኝነት ነው እንግዲህ እግዚአብሔር እንዲያስብለት ያደረገው። ይህ አኗኗር ለአዳም መልካም አልነበረም፤ ለአዳም መልካም የሚሆን ረዳትና አጫዋች እርሱን የሚመስልና የእሱን ኑሮ የሚካፈል ሊኖር አስፈለገው። ያ ካልሆን በቀር አዳም ደስተኛ ሊሆን አይችልም። ስለሆነም እግዚአብሔር አንድ በመሆን ሴትና ወንድ ሆኖ የፈጠረውን አዳምን በላዩ ላይ እንቅልፍ እንዲመጣ አድርጎ ከእርሱ ከጎኑ ረዳት የምትሆነውን ሴትን ሰጠው። ይህ እንግዲህ የመጀመሪያው ጋብቻ ስለሆነ አዳምና ሔዋንን የገነት ሙሽሮች ብለን ልንጠራቸው እንችላለን። የአዳምና የሔዋን አባት የሆነው እግዚአብሔር በብቸኝነት ጠውልጎና ተስፋ ቆርጦ ለነበረው አዳም የሔዋንን እጅ ጎትቶ ሲሰጠው ከየት እንደመጣች ስለተረዳ «ሥጋዋ ሥጋዬ አጥንቷ አጥንቴ» በማለት ደስ ብሎት ኑሮውን ጀመረ። ስለዚህ ነው ጋብቻ የተፈጠረ እንጂ የተፈለሰፈ አይደለም የምንለው።

የጋብቻ አመሠራረት ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን ዓላማው ደግሞ ሁለት ታላለቅ ነገሮችን የያዘ ነው። እነርሱም፦

1) ለመረዳዳት 2) ለመብዛትና ለመባዛት ናቸው።

እነዚህን መሠረት በማድረግ የተፈጸሙ ጋብቻዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ስለሆኑ ከነሱ ውስጥ ጥቂቶቹን መርጠን እንመለከታለን።

፩) ስለ አብርሃምና ስለ ሣራ የመጀመሪያ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት መጽሐፍ ቅዱስ ዝርዝር መግለጫ አይሰጥም። ነገር ግን የአብርሃም አባት ታራ የአጎቱ ልጅ ሎጥና አብርሃም ከነሚስቱ ከሀገር እንደተሰደዱና በከነዓን ምድር እንደኖሩ ይገልጻል። በዚህም በሚኖሩበት ሀገር የአብርሃም አባት ታራ ከሞተ በኋላ ሎጥና አብርሃም ከነሚስቱ ለትንሽ ቀን ቆይተው በችግር ምክንያት እንደተሰደዱም እንመለከታለን። በዚህ በግብጽ ሀገር ሲኖሩ አብርሃምና ሣራ የሚፈተኑበት ነገር መጣ። ይህም የአብርሃምን ሕይወት የሚጠይቅ የሣራ ውበት ነበር። ሣራ የአብርሃምን ሕይወት ለማትረፍ በሕይወቷ አስቸጋሪ የሆነውን ነገር ማድረግ ነበረባት። የዚህን ሙሉ ታሪክ በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፲፪፥፲፩-፲፫ አብርሃም ወደ ግብጽ ሲቀርብ ሚስቱ ወንድሜ ነው እንድትል ሲዋሽ እንመለከታለን(ከቁጥር ፲፫- እስከ ፲፮)። በዚህ ምክንያት የአብርሃም ሕይወት እንደሚተርፍ አብርሃም ምኞቱ ነበር። ስለሆነም አብርሃም በዋሸው መሠረት ሚስቱን እኅቴ ናት ብሎ ለፈርኦን ሰጠ (ከ፲፯- ፳)። እግዚአብሔር ግን የአብርሃምን ውሳኔ ተቃወመ። አብርሃም ሚስቱን ለፈርኦን የሰጠበት ምክንያት ውበትዋ እጅግ መልካም ስለነበር ባልዋ ከሆነ እርሱን እንደሚገድሉት ስለተረዳ ነው። በሌላ መልኩ የእሷን ውበት ለእርሱ ሕይወት ተጠቀመበት። የሚገርመው ግን ይህች አስገራሚ የሆነች እናት እንደ ውጫዊው አካልዋ ሁሉ ውስጣዊ እምነትዋ ከፍተኛ ስለነበር ለባልዋ አልታዘዝም

ሳትል ከዚህ እንዲያድናት ለአምላኳ መጸለይ ነበረባት። ስለሆነም ከውጪያዊ ውበትዋ ይልቅ ውስጣዊና ሃይማኖታዊ ውበትዋ በለጠና በእግዚአብሔር ዘንድ ተወዳጅ ሆና በአሸናፊነት ስትወጣ እንመለከታለን።

ብዙዎቻችን የአብርሃምን ውሸት እንቃወማለን። እርግጥ ነው አብርሃም ዋሽቷል። አዎ! በመዋሸቱን እግዚአብሔር አጋልጦታል። ምክንያቱም እግዚአብሔር እርሱ በወሰደው እርምጃ አልተስማማምና። ይህ ጋብቻ በእግዚአብሔር እጅ ላይ የተጣለ ጋብቻ ነበር። በተለይም ሣራ በቤተ ሰባዊ አስተዳደር ለባልዋ ታዘዘች። በሃይማኖታዊ አካሄዷ ደግሞ ለሀብት ሳትሳሳ በእግዚአብሔር ፊት በመልካም አካሄድ ሄደች። ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔር የዘለዓለም እቅዱ የሆነውን የደኅንነትን ነገር በእርስዋ በኩል እንዲከናወን በረከትን ተሞላች። ዘፍ ፲፰፥፮ ፤ ምዕራፍ ፲፯፥፩-፲፯ እነዚህ ማረጋገጫዎቻችን ናቸው።

ብዙ ባለ ትዳሮች ከእነዚህ የትዳር ጓደኞች የሚማሩት አለ። ሣራ ለአብርሃም መታዘዝዋ እና ትዳራቸውንም በእግዚአብሔር እጅ ላይ መጣላቸው መልካም ጎናቸው ሲሆን በትዳራቸው ያጋጠማቸውን ችግር ደግሞ በቦታው እንመለከታለን።

፪) ሁለተኛው የአብርሃም ልጅ የይስሐቅ የርብቃ ጋብቻ ነው። የዚህ ጋብቻ አፈጻጸም እጅግ የተለየ ነው። አብርሃም ልጁ ከአሕዛብ ወገን እንዲያገባ አልፈለገም። ለዚህም ምክንያት በወኪል ጋብቻው ሲፈጸም እንመለከታለን። ይህም በቤተ ሰብ አመራር ላይ ችግር ነበረው። የጋብቻው አፈጻጸምም በዘፍጥረት ፳፬፥፲፮ ላይ ተዘርዝሯል።

፫) የያዕቆብ እና የራሔል ጋብቻ በጥቅምና በውበት ወጥመድ ውስጥ የገባ በቤተ ሰብ አስተዳደር ላይ ከፍተኛ ምሳሌነት ያለው ጋብቻ ነው። ይህንኑ በዚሁ በዘፍጥረት ላይ እናገኘዋለን። በጥቅም ላይ የተመሰረተ ጋብቻ ያስከተለውን ችግር ወደፊት እንመለከተዋለን።

፬) ከሰው አእምሮ በላይ የሆነው በእግዚአብሔር እቅድና ዓላማ መሠረት የተካሄደው ከተሟጠጠ ተስፋና ሕልውናን ያንሰራራው የሩትና የቦኤዝ ጋብቻ ነው። በመሣፍንት ዘመን ከተፈጸመው ታሪክ ውስጥ የሚነግረን መጽሐፈ ሩት የዚህን ጋብቻ ሥነ ሥርዓት ከየት እንዴት እንደሄደ በሚያስደንቅ ሁኔታ ዘርዝሮታል (ምዕራፍ ፬፥፲፩-፲፪)። የጋብቻው አፈጻጸም እንዴት እንደነበረ በሚያስደንቅ ሁኔታ ይነግረናል። እግዚአብሔር የሁለቱን የትዳር ጓደኞች ሁኔታ እንዴት እንዳካሄደው በመገረም ካልሆነ በስተቀር በምርምር ልንረዳው አንችልም። ይህ ጋብቻ በእግዚአብሔር የተካሄደ ስለነበር ምንም ዓይነት እንከን አልወጣለትም። ስለ ሩት እምነትና ታማኝነት ምዕራፍ ፩፥፲፮-፲፯ የሚከተለውን ይነግረናል። «ሩትም፥ ወደምትሄጂበት እሄዳለሁና በምታድሪበትም አድራለሁና እንድተውሽ ከአንቺም ዘንድ እንድመለስ አታስቸግሪኝ፤ ሕዝብሽ ሕዝቤ አምላክሽም አምላኬ ይሆናል። በምትሄጂበትም ሥፍራ እሞታለሁ፥ በዚያም እቀበራለሁ፤ ከሞት በቀር አንቺንና እኔን አንዳች ቢለየን እግዚአብሔር ይህንን ያድርግብኝ እንዲህም ይጨምርብኝ አለች።»

፭) በአምስተኛ ደረጃ ላይ የምናየው በሰው ፍላጎትና በጥቅምና በፖለቲካ ላይ የተመሠረተ ጋብቻ ነው። ይኸውም የአክአብና የኤልዛቤል ጋብቻ ነው። እነዚህ ሰዎች ጋብቻን
በጥቅም ላይ መሥርተው በፖለቲካና በስልጣን በመመካት ባደረጉት ክፉ ሥራ አልዛቤልም ባልዋም በአሳዛኝ ሁኔታ እንደሞቱ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ጠቅላላ ታሪኩ በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ምዕራፍ ፳ ከቁጥር ፲፮ ጀምሮ እስከ ፳፮ ያስረዳል። እርሷ የወለደቻት ልጅ እንኳን እንዴት ዓይነት ክፉ እንደነበረች ሁለተኛ ነገሥትም ምዕራፍ ፱ ቁጥር ፴ እስከ ፴፯ ላይ ያስረዳናል።

በአጠቃላይ ጋብቻ ከእግዚአብሔር የተሰጠ በእግዚአብሔር የተከበረ ለሰው ልጅ የደስታ ምንጭ ሲሆን በአግባቡ ካልተያዘ ደግሞ ከባድና አስቸጋሪም ነው። እስከ አሁን ያየነው የጋብቻን አመሠራረትና ዓላማ ነው።

<u>አፈጻጸሙ፥</u> ጋብቻ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ በመሆን ምስጢረ ተክሊል በመባል ይታወቃል። ጋብቻ በአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ክብረ በዓላት ከሚባሉት አንዱ ነው። ምስጢረ ተክሊል በመባል የሚታወቀውም ወይም የጋብቻ ጸሎት በመባል የሚታወቀውም ለዚሁ ነው። የሚፈጸመው በጳጳሳትና በካህናት ብቻ ነው። ዲያቆናት ረዳት ካልሆኑ በስተቀር ራሳቸውን ችለው ሥርዓተ ጋብቻን አያስፈጽሙም። የሚጸለየው ጸሎት፣ የሚነበቡት ቅዱሳት መጻሕፍት ከቅዳሴ ጋር እኩል ነው። በማጠቃለያም በዓሉ የቤተ ክርስቲያን ይሆን ዘንድ በቅዳሴ ይደመደማል። ሙሽሮቹ ወይም ተጋቢዎቹ በዚሁ ዕለት ሥጋውና ደሙን ይቀበላሉ። ምክንያቱም በዓሉ የነሱ ስለሆነ። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋብቻ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ስለሆነ በሥጋ ዝምድና አንድ የሆኑ ሰዎች ሊያደርጉት የማይችሉት፣ በእድሜ ብዛት ልዩነት፣ በእምነት ልዩነት፣ በባሕል እና በቋንቋ ሁሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግለት የሚገባ ሥርዓት እንደሆነ ታስተምራለች።

ይሄ ሆኖ ሳለ ግን በአሁኑ ጊዜ በስፋት የሚታየው የወጣቱ ቤተ ክርስቲያንን እና ሥርዓትዋን የመተቸት መንፈስ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። አንዳንዶቹ ተክሊል ይደረግልን ቅዳሴ ይቅርብን፣ ቀለበቱ ይደረግልን አክሊሉ ይቅርብን ብለው ይጠይቃሉ። ለምን ተብለው ሲጠየቁ የሚመልሷቸው መልሶች አንዳንድ ጊዜም ያሳዝናሉ። ሌላ ጊዜም ያስቃሉ። የሚሉትም በዚህ እድሜዬ ሥጋ ወደሙ ተቀብዬ እንዴት ሊሆን ይችላል? ሲጋራ አጨሳለሁ፣ እጠጣለሁ፣ ክፉም እናገራለሁ አንዳንድ ጊዜም «ሲስተሙ ይሄ ነው» በማለት መልስ ይሰጣሉ። እንግዲህ እነዚህ ወጣቶች ፍላጎታቸው ቤተ ክርስቲያኒቱ በእነሱ ሃሳብ ወይም ፈቃድ ተስማምታ በእነሱ አባባል የዚህ ዓለምን ኑሮ (በቤተ ክርስቲያን ቋንቋ ኃጢአት) በሕግ ቋንቋ ወንጀል እንዲሠሩ እንድትፈቅድላቸው ነው። የሚያሳዝነው ግን አንዳንድ ካህናት ሳይቀር «ወጣቱን ቀስ አድርጎ ነው መያዝ» «ምንም አይደል» በማለት በወጣቶቹ ሲሄዱ ይታያሉ። አንዳንድ ወላጆችም ልጆቻቸው ለትዳር ሲዘጋጁ ቆርበው እንዳይጋቡ ሲያከላክሉ ይታያሉ። ለልጆቻቸውም አማላጅ ሆነው ጭምር ይቀርባሉ። ይህ ትክክል ስላልሆነ ተጋቢዎች ሊያስቡበትና የቤተ ክርስቲያንን መንገድ ሊከተሉ ሥርዓቱንም ሊጠብቁ ይገባል።

ጋብቻ መልካም ሆኖ ሳለ ለምንድን ነው በዓለም ላይ ብዙ ፍቺ የምናየው? ባልና ሚስት በመፋታታቸው ምክንያት ልጆች ያለ አሳዳጊ ሲቀሩ የምናየው ለምድን ነው? በፍቺ ምክንያት ሰለባ የሆኑ ወደማይገባ ድርጊት ውስጥ ሲገቡ የምናየው ለምንድን ነው? ጋብቻን በአግባቡና በእግዚአብሄር ዳኝነት ካልያዙት ከባድ ጎን እንዳለው መገንዘብ ይኖርብናል። ስለሆነም ጥያቄው «ጋብቻ እንዲጸና እና ልጆች ያላሳዳጊ እንዳይቀሩ የትብረተሰብ መዋቅርም እንዳያዛንፍ ምን ማድረግ አለብን?» የሚለው ነው። ስለሆነም ችግሩን በመጠኑም ቢሆን እንድንረዳው ለጋብቻ መሰናክል የሆኑትን አበይት ነጥቦች ከዚህ በመቀጠል እንመለከታለን።

፩ኛ) በቤተ ሰብ አመራር ላይ ማነው የበላዩ ወይም ደግሞ በቤተ ሰብ አመራር ላይ የበላዩን በሚመለከት በዘመናችን በተለይም በምዕራቡ ዓለም ከፍተኛ አጠያያቂ ሆኖአል።ምክንያቱም ወንዶች የተሰጣቸውን የቤተ ሰብ ኃላፊነት ሴቶችን ለመጨቆን ስለተጠቀሙበት ሴቶች እንዳይበደሉ ለመከላከል የወጡ ሕግጋት ዓላማውን ስቶ ወንዶች በቤተ ሰብ ላይ የበላይ እንዳይሆኑ የአባ ወራነቱን ቦታ እንዲለቁ እያስገደደ መጥቷል። ሴቶችም መብታቸውን ለማስጠበቅ በሚያደርጉት ግፊት በማወቅም ባለማወቅም የቤተ ሰብን መሰረት የሚያናጋ ሥራ ሲሠሩ ይታያሉ። ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ነገር ምን ይላል?

የመጀመሪያዎቹን የገነት ሙሽሮች ስንመለከት ከጋብቻው ሥነ ሥርዓት በኋላ ብዙ ጊዜ በደስታ የቆዩ አይመስሉም። ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፫ ከቁጥር ፩ ጀምሮ ያለውን ስናይ ሔዋን በአመራር ላይ የበላይነት ወስዳ ከእባብ ጋር ባደረገችው ውይይት አትብሉ የተባለውን ፍሬ ለመብላት እግዚአብሔርና ባልዋን ሳታማክር እርሱንም አሸንፋ የእስዋ ተባባሪ አድርጋ በተወሰደው እርምጃ ነው ችግሩ ሁሉ የመጣው። ሆኖም ግን ተጠያቂ የሆነች ሔዋን ሳትሆን አዳም ነበር። ይኼም የሚያሳየው

የቤተ ሰብ ተጠሪ ወይም አባ ወራ የወንዶች እንደሆነ ነው። እሷ የወሰደችውን ኃላፊነት እግዚአብሔር ለእሷ አልሰጠም። ታላፊነቱ የተጣለው አመራሩን ለቆ እንደውም በሷ ተሸንፎ በተገኘው በአዳም ላይ ነው። ይህ የቤተ ሰብ ኃላፊነት መዛባት በሰው ልጅ የሕይወት ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ለውጥ አመጣ፤ ለመልካም ሳይሆን ለመጥፎ። ይህ ባለንበት ዘመን በትክክል ሲሠራ እንመለከታለን።

የጋብቻ አስቸጋሪ ጎን የሚጎዳው ሁለቱን ተጋቢዎች ብቻ ሳይሆን ቤተ ሰቦቹን ጭምር ነው። አጥንት የሚሰብር ስድብና አእምሮን የሚነካ ነገር በሁለቱ ተጋቢዎች ብቻ ሳይሆን በቤተ ሰቦችም መካከል ይተላለፋል። አዳም ያደረገው በትክክል ይህን ነበር ማለት ይቻላል። አትብላ የተባለውን «ለምን በላህ?» ተብሎ ሲጠየቅ እግዚአብሔርን የመዝለፍ ያክል «አንተ የሰጠኸኝ ሴት» በማለት ጥፋቱን ወደ እግዚአብሔር ሲያዞር እንመለከታለን።

እንዲያ የተዋበ ጋብቻ እያልን ያወሳነው የአብርሃምና የሣራ ጋብቻም የዚህ ዓይነት ችግር ገጥሞታል። ሣራ የራሷን ሕይወት እንኳን እስከ መስጠት ደርሳ የታዘዘችለትን አብርሃምን ከዚህም የተነሳ ያከበራትን እግዚአብሔርን ሳትጠይቅ «ልጅ ትወልጃለሽ» ተብሎ እየተነገራት ከነፈርኦን እጅ ፈልቅቆ ያወጣትን አምላኳን ተጠራጥራ አብርሃም ከገረዷ እንዲወልድ ወሰነች። አብርሃምም እንደዚያ ለሰው እስከሚሰጣት ድረስ ያዘዛትን ሚስቱን ስልጣኗ እስከ ምን ድረስ እንደሆነ ሳይጠይቅና ሳይመካከር እግዚአብሔርንም ሳይጠይቅ የሷን ትዕዛዝ ተቀብሎ ባደረገው ድርጊት የቤተ ሰቡ ሁኔታ እንዴት አሳዛኝ ደረጃ ላይ እንደደረሰ ኦሪት ዘፍጥረት ፲፮፡፩-፮ ያስረዳናል።

የያዕቆብ ታሪክም ይኸው የቤተ ሰብ አመራርን መልቀቅና በርብቃ መመራት ቤተ ሰብ ላይ ከፍተኛ ችግር እንዳመጣና በበረከት አሰጣጥ እራሱ እሱ ያለው ሳይሆን ሚስቱ ያለችው ሲደረግና በልጆቹ ላይ ብጥብጥ ሲፈጥር እንመለከታለን። ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፳፯፣፲፰-፵ ድረስ ያለው ታሪክ ይህን ያስረዳል። ያዕቆብ እንደ ሌላው ብልጠቱ ሁሉ በሚስቶቹ ላይ ከፍተኛ ስልጣን ነበረው። እንደ አማትዬው ጣልቃ ገብነትና እንደ ሚስቶቹ የእርስ በርስ ቅናት ደካማ ቢሆን ኖሮ የቤተ ሰብ አመራሩም በምን ዓይነት ችግር ይወድቅ እንደነበር ለመገመት አያዳግትም።

፮) በቤተ ሰብ አመራር ኃላፊ ማን ነው?

በብዙ እኅቶች የሚጠየቀው ባል የሚስት እራስ ነው። ሚስት ደግሞ ለባል መታዘዝ አለባት የሚለውና በተለይም ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ራሷ እንደሆነ ባልም የሚስት ራስ ነው የሚለው ነው። ይህንን ትርጉም ብዙ ሰዎች ሲቸገሩበት እንመለከታለን። በደንብ ሲታይ ግን በቤተ ክርስቲያንና በክርስቶስ መካከል ያለውን የበላይነት የጭቆና እንዳልሆነ ሁሉ በባልና ሚስት መካከል ያለው የበላይነትም በቀጥታ የክርስቶስን ምሳሌነት ነው መከተል ያለበት። ምክንያቱም ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ወደዳት የሚባለው ራሱን በመስጠት እንጂ ወይም በደሙ በመግዛት እንጂ የራሱ ያደረጋት ከእስዋ በመውሰድ አይደለምና። ስለዚህም በኤፌ ፭፥፳፪-፴፫ በሚገባ ተገልጿልና የተጻፈውን መመልከት ይቻላል። በባልና በሚስት መካከል ያለው የአመራር ሁኔታ መካሄድ ያለበት በዚህ ደረጃ ነው። በዚህ እስከተመራን ድረስ ጋብቻ ችግር አይኖረውም።

፯ኛ) በማንነት ላይ ያልተመሠረተ ማንነት

እስከ አሁን እንደሚታየውና እንደተጠናው ለጋብቻ እንቅፋቶች ከሆኑት ነገሮች አንዱ ከጋብቻ በፊት ማንነትን በትክክል አለመግለጽ ነው። በተለይም ከጋብቻ በፊት በሚደረግ ልምምድ ላይ ተመስርቶ የሚካሄድ ጋብቻ ውጤታማነቱ ከግማሽ በላይ አጠራጣሪ ነው። ምክንያቱም ምንድን ነው? ወንዱም ሴቲቱ እንዳታመልጠው የእሱ ያልሆነውንና የእሱነት ባሕርይ የማያመነጨውን በማሳየትና በመሆን ሴቲቱን የእሱ ለማድረግ ይምክራል። ይሄም በብዙ መልክ ሊሆን ይችላል። ገቢን፣ እውቀትን፣ ቤተ ሰብን፣ ዘርን አጠቃላይ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ያጠቃልላል። ሴቷም በበኩሏ ይህን ዓይነት ሚና ልትጫወት ትችላለች። ይሄ ጉዳይ ለስድስት ወር ለዓመት ወይንም ለሁለት ዓመት ሊቆይ ይችላል። ሰው ግን ዕድሜ ልኩን ሌላ ሰው ሆኖ ሊኖር አይችልምና ተጋቢዎች ወደ እውነተኛ

መ) የትዳር ኃላፊነትን መውሰድ

የመጨረሻውና ዋናው የትዳር ጓደኞሞች ሁልጊዜ ባለ ትዳር ሲሆኑ የየራሳቸውን ኃላፊነት መውሰድ አለባቸው። ያም ከእያንዳንዳቸው የግል ጉዳይ ጀምሮ እስከ ቤተ ሰብ ይሄዳል። ከትዳር በፊት የነበረው የአኗኗር ስልት በሙሉ መቀየሩን መገንዘብ ያስፈልጋል። ያም የአባ ወራው ወይም የእመቤቲቱ ባሕርይ ሳይሆን የጋብቻው ባሕርይ የሚያመጣው ወይም የሚጠይቀው ነው። ከሚበሉት ምግቦች ጀምሮ እስከሚለበሱት ልብሶች፤ ከሚንጠለጠሉ የግርግዳ ጌጦች አንስቶ እስከ ምግብ ቤት ዕቃዎች ድረስ ሌላ ሌላውም ሁሉ በምክክር መሆን መቻል አለበት። ትዳር በሚጠይቀው በማንኛውም ሁኔታ ወይም በሚመጣ ችግር ዙሪያ ግልጽ በሆነ መንገድ ስሜትን እየገለጹ መወያየት ያስፈልጋል። ይህ ማለት አንዱ ለሌላው መሰጠትንና ሁለቱ አንድ ሆነው መኖርን አንዱ የሌላውን ስሜት እያከበረ የራሱንም ኃላፊነት እየተወጣ መኖር አለበት ማለት ነው።

## ማጠቃለያ

ከመጀመሪያው ጀምሮ እንዳየነው ጋብቻ ለሰው ልጅ ትክክለኛ ሕይወትን ሰጭና ማንነትን ገላጭ ነው። ጋብቻ ከዝሙት ለመራቅና ከመንገላታት በአጠቃላይ በዚህ ዓለም በነጠላ ከመኖር የሚያድን ታላቅ ጥምረት ነው። ስለሆነም ሰው ስለፈለገው ሳይሆን ለሰው ስለሚያስፈልግ ከእግዚአብሔር የተሰጠ የበረከት ስጦታ ነው። ለዚህም ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምድራዊ አገልግሎቱን ሲጀምር በሠርግ ቤት ተገኝቶ ውኃውን ወደ ወይን የለወጠው (የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፪ ከቁጥር ፩ ጀምሮ)። ለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህ ምስጢር ታላቅ ነው በሚል በአስደናቂ አነጋገር የተረጎመው። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ጋብቻ ባስተማረበት አንቀጹ የሁለቱን ባለ ትዳሮች የኑሮ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የቤተ ሰብንና የማኅበረ ሰብን መዋቅርና የእያንዳንዱ ኃላፊነት እስከ ምን ድረስ እንደሆነም ጨምሮ አብራርቷል። ይህም ኃይለ ቃል በኤፌሶን ፮፥፲-፲፰ ድረስ ተጠቅሷል። ልጆች ለወላጆቻቸው ወላጆችም ልጆቻቸውን ማክበር እንዳለባቸው፤ አገልጋዮች ለተገልጋዮቻቸው ተገልጋዮችም ለአገልጋዮቻቸው ለእግዚአብሔር እንደሚገዙ ያህል እንዲገዙ አዝዟል። ሐዋርያው ይህንን ትእዛዝ ሲሰጥ በቤተ ሰብና በማኅበረ ሰብ አመራር ላይ ችግር እንደሚኖር ስላወቀ መፍትሔውን ጭምር አስቀምጧል። የቤተ ሰብም ሆነ የማኅበረ ሰብ መናጋት ችግር መንስኤው ከሥጋና ከደም ሳይሆን ከክፉ መናፍስት በመሆኑ መፍትሔ ሊገኝ የሚችለው ከእግዚአብሔር ብቻ እንደሆነም አብራርቷል።

ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር ቃልና እንደ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ከሄድንና ቃል ኪዳናችን ከሰው ጋር ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔርም ጋር እንደሆነ ባለመዘንጋት ኑሯችንን ማስተካከል ይገባናል።

*በአባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ .*